-፩-

# ማንን ነው የምናምነው

## ከበልጅግ አሊ

ሃገራችንን በተመለከተ ወቅታዊ ዜናን ለማግኘት ከድኅረ ገጽ ወደ ድኅረ ገጽ እየተዘዋወራችሁ እንደኔ ታነቡ ይሆናል። በሁሉም በኩል ሚዛኑን የጠበቀ ዜና ለማግኘት ውሸት የተመላበትን ዘገባ የሚያቀርበውን ድኅረ ገጽ ሳይቀር ትመለከታላችሁ። ያ አይረባም የምትሉት ድኅረ ገጽ አንድ ቁም ነገር ያለውን ጉዳይ እንደው እንደዋዛ አስፍሮ ብታገኙ ምን ትላላችሁ? ዕጹብ ድንቅ ይህም አለ ለካ ብላችሁ ታልፉታላችሁ? በተለይ ደግሞ የሠራሁት ተግባር አይጋለጥም ብሎ በወንጀሉ ተባባሪዎች ተከቦ የሚኮፈስ ግለሰብ ከሆነ ደግሞ ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ማለታችሁ አይቀርም። ለማንኛውም እውነቱ ተጣርቶ እንዲወጣ መፈለጋችሁ አይጠረጠርም።

በማይረባው ድኅረ ገጽ ላይ የተጻፈውን ድኅረ ገጹ አይረባም ብሎ እውነቱ ተደብቆ መቅረት አለበት ብሎ የሚያምን ይኖራል ብዬ አላምንም።ይህ ፅሁፍ ደግሞ የተኮፈሰውን ግለሰብ የሚጋልጥና መፀሐፍን ያጣቀሰ መረጃ ላይ የተመረኮዘ ከሆነ ደግሞ ያወጣውን  ድኅረ ገጹን በመስደብ ብቻ ነፃ አይወጣም።ብዙ አንባቢ ስለሚያነበው ፣ ንፁህነትን በማስረጃ ማቅረብ እንጂ ሌላ የሚያዋጣ  የለም ። በተለይ ድኅረ ገፁ ላይ የፃፈው የተኮፈሰው ግለሰብ  የቅርብ ጓደኛ. የጥፋት መልዕክት ተባባሪህ፣ አብረን አደረግነው ባይ ከሆነ ደግሞ አይጣል ነው።እነርሱ ናቸው እንዲህ ያደረጉኝ ብሎ የተለመደውን የፖለቲካ ድርጅት አባላት እንኳ ማሳበብ አይቻልም።  ጉድ ፈላ ማለት ነው። ነፃ ጋዜጠኞችን ያጋልጥልን ነበር፣ እነርሱን ለማሰር ይተባበረን ነበር፣ ከተባለ ደግሞ ወደ ወንጀል መሄዱ ነው። በእስር የተሰቃዩት ጋዜጠኞች ይታሰቡናልና የንጹሃን ስቃይ በከንቱ እንዳይቀር እውነቱን መፈለጋችን ሁልግዜም የማይተው ጉዳይ ይሆናል።

ይህ ሁሉ ሃተታ ምንድነው ልትሉኝ ትችሉ ይሆናል።ባለፉት ቀናት የኢትዮጵያን ሪቪው የሚባለውን ድኅረ ገጽ ሳነብ ይህን ዓይነት ሁኔታ ነበር የደረሰብኝ። ጉዳዩ እንደዚህ ነው። ከድኅረ ገጽ ወደ ድኅረ ገጽ ስዘዋወር ብዙም የማልጎበኘው ኢትዮጵያን ሪቪው ላይ ደረስኩ። An explosive book by a former TPLF insider  የሚል ርዕስ ተመለከትኩ።ደግሞ የትኛው ወያኔ ነው መፅሐፍ የፃፈው ብዬ ማንበብ ጀመርኩ። ተስፋዬ ገብረ አብ የሚባል የወያኔ ባለሥልጣንና ጋዜጠኛ የነበረ ነው።ድኅረ ገጹ መፅሐፉ  በውስጡ የሚደነቅ የወያኔን ወንጀል ይዟል ይላል። ከመፅሐፉ ላይ የተቀነጨበ ሰላለ ማንበብ ጀመርኩ።

አጀማመሩ ራስን ለማዳን ጥረት በማድረግ ላይ የተመሰረተነው ይጀምራል።ለወያኔ ሳገለግል ቆይቼ በኮበለልኩ ግዜ ግማሽ ሚሊዮን ብር ይዘህ ነው ተብዬ እታማለሁ ይህ ሃቅ አደለም ብሎ ለማስተባበል ይሞክራል።እኔ የምመራው ድርጅት በባንክ ምንም ገንዘብ የለውም ባይ ነው። ፀሐፊውን የሚቃወሙ ሌሎች ወያኔዎች የነበሩ ገንዘቡን ከወያኔ ሰርቆ መምጣቱን በኢትዮ ሚዲያ በሚባለው ድኅረ ገፅ እንዳጋለጡት ነው የሚፅፈው። ፀሐፊው የሚለው የኢትዮ ሚዲያ ባለቤትም በጉዳዩ ውስጥ እንዳለበት ነው። ግልፅ አድርጎ በቂም በቀል ተነሳስተው ወነጀሉኝ እንጂ እኔ አልወሰድኩም ይላል ።ግሩም ድንቅ እያልኩ ማንበብ ቀጠልኩ ፀሐፊው ስለ ኢትዮ ሚዲያ ባለቤት ስለሆኑት አብርሃ በላይ የፃፈውን ስመለከት ደነገጥኩ። ዐይኔ ፈጠጠ ። ማመን አቃተኝ።ፀሃፊው በወያኔ አስተዳደር ውስጥ የአቶ አብርሃ በላይ አለቃ ነኝ ባይ ነው። ቂም በቀላችን የተጀመረው ወያኔን ስናገለግል ነበር የሚለው አቶ ተስፋዬ ገብረ አብ መረጃ የተባለውን ሁሉ አቅርቧል።እማኝም አቶ አማረ አረጋዊን አድርጓል።

ከሁሉ የሚገርመኝ ፀሐፊው " እኛ ወያኔዎች አዲስ አበባ በገባን ግዜ እኔ ፕረስ መምሪያ ሃላፊ ሆኜ ስመደብ ፣ ፕረስ መምሪያ ላይ በፈቃደኛነት ለወያኔ አባልነት ራሱን የመለመለ ቀዳሚው ሰው አብርሃ በላይ ነበር ብሎ የፃፈው ነው። ለመሆኑ ማንን ነው የምናምነው? ፀሐፊው አብርሃ በላይ ምንም የማይረባ ለግል ጥቅም የቆመ እንጂ አቋም የሌለው ቢሆንም ከወያኔ ያልተባረረበት ጉዳይ የሙሉጌታ ሉሌ ደጋፊዎች(ማለትም የወቅቱ የነፃው ፕረስ አባላትን ማለቱ ነው) የሚባሉትን ጋዜጠኞች ስም ዝርዝር ፅፎ ያቀረበልን ባለውለታችን ስለነበር ልናስቀይመው አልፈለግንም ይላል።

ከዚህ ፀሃፊ ምስክርነት ስንነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት የሆነ ግማሽ ሚሊዮን ብር እንደ ዋዛ መጫወቻ ሆኖ አንተ ነህ ፣ አንተ ነህ በሚል ቀልድ ቀልጦ መቅረቱን እንመለከታለን።መቼም ሌባ ሲሰርቅ አይጣላም ሲከፋፈል እንጂ። ለእኔ አቶ ተስፋዬ ገብረ አብም ይሁን አቶ አብርሃ በላይ ግልፅ መረጃቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።የዚህ የገንዘብ ምሥጢር የወጣው በጥቅም ጠብ ምክንያት እንጂ ምሥጢሩ እንደተደበቀ ይኖር ነበር። አንድ ሃቅ ያለው ግማሽ ሚሊዮኑ ብር ጠፍቶአል። የወያኔ አባላት ከላይ እሰከታች በስርቆት ላይ መሆናቸውን የታወቀ ነው።

የነፃውን ፕረስ አባላት ማጋለጥን በተመለከተ የተፃፈውን ስንመለከት ደግሞ አቶ አብርሃ በላይ በወንጀለኝነትን ሊስጠይቅ የሚችል ነው ብዬ አምናለሁ። እውነት አቶ አብርሃ  ለዚህ ክስ መልስ አላቸው? ካላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መግለጥ ይኖርባቸዋል። እንደሚታወቀው ይህ ተግባር ተፈፀመ የተባለበት ወቅት ጋዜጠኞች በገፍ የሚታሰሩበት ፣ የሚገረፉበትና ፣ የሚሰቃዩበት ፣ ደብዛቸው የሚጠፉበት ወቅት ነበር።  በዛ ወቅት ለተፈፀመው ኢሰብአዊ  ድርጊት ኃላፊነትን ወስዶ የተናገረ የለም። ይህ አቶ ተስፋዬ ግብረ አብ የተባለው ግለሰብ  የሰጠውን ሃሳብ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚጠይቅ ክስ ዝም ልንለው አይገባም። አቶ ተስፋዬ  እኔ አደለሁም አቶ አብርሃ ናቸው የሚለው እውነቱን ወይም ውሸቱን ሊሆን ይችላል። ጥያቄው ግን አቶ አብርሃ በላይና አቶ ተስፋዬ ለወያኔ ሲያገለግሉ በእስር ቤት የተሰቃዩትን

ጋዜጠኞች ብዙ መሆናቸው እርግጥ ነው። በእስር በሽታ ላይ የወደቁ፣ የተገረፉና የተሰቃዩ ብዙ ናቸው።ስለዚህ የዚህ እውነተኝነት መታወቅ በጣም አስፈላጊ ነው እላለሁ። አቶ አብርሃ በላይ ወያኔ ውስጥ በነበሩበት ግዜ የሰሩትን በትክክል ካላጋለጡ ሁልግዜ ከተጠርጣሪነት አንድ ቀን ደግሞ በግድ ከሚመጣ የታሪክ ፍርድ አያመልጡም። ይህ ፍትህን መሻት እሳቸውን ብቻ አደለም የሚመለከተው አቶ ስዬ አብርሃን ፣ አቶ ገብሩ አስራትን ፣ እንዲሁም ሌሎቹን ከወያኔ ወጥተው ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሁሉ እውነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካላጋለጡ በስተቀር በተቃዋሚነት ልንቀበላቸው አይገባም።

የወያኔ አባላት ከወያኔ ተለይተናል በሚሉበት ግዜ ስለወያኔ ሚውጢራዊ አሰራር መግለጥ ይኖርባቸዋል። እነማን በተቃዋሚዎች ውስጥ የተሰገሰጉ የወያኔ ሰላዮች እንደሆኑ ማጋለጥ አለባቸው። ወያኔ እንዴት ነው በሃገር ውስጥ የስለላ ሥራውን የሚያኪያሂደው ? እነማን ናቸው ከወያኔ በሚስጥር የሚከፈላቸው? በድብቅ የታሰሩ እስረኞች የት ናቸው? ቁጥራቸውስ ስንት ነው? የት ነው የድብቅ እስረኞች የሚገኙት?

እነዚህንና እነዚህ የመሳሰሉ ጥያቄዎች መመለስ ለፀረ ወያኔ ትግል በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ይህንን ሳያጋልጡ በአንድ ወገን ወያኔን እየወደዱ በሌላ ደግሞ ተቃዋሚ መሆን አይቻልም።

ይህ አቶ ተስፋዬ የፃፈውን ስንመለከት እነ ስዬ ስንት ጉድ ሊነግሩን እንደሚችሉ ትገምታላችሁ? የስንት ንፁሃን ደም በከንቱ ፈሶ መቅረት እንደሌለበት መገመትስ እንችለለን? በትግራይ ውስጥ በተሠሩ እስር ቤቶች የሚማቅቁት እነ ፀጋዬ ደብተራው? ያሉበት የማይታወቀው ጋዜጠኞችስ ?

እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች በምናቀርብበት ግዜ እንደተለመደው አንዳንድ አንጃዎችና ባንዳዎች መጮሃቸው አይቀርም። በተለይ እነዚህ ከወያኔ ወጣን የሚሉትን እንደ ጀግና ሲክቡ የነበሩት ወገባቸውን መስበቃቸው አይቀርም። ምክንያቱ ግልፅ ነው የወያኔ የድብቅ የደሞዝ መክፈያ ሰነድ ከተጋለጠ የስንቶች አወናባጆች ስም መገኘቱ አይቀርምና ነው። እነ ሰዬን ሳያጋልጡ መቀበሉን መቀስቀስና መታገል የአንጃዎች ቀዳሚ ተግባር የሆነውም ለዚሁ ነው። ግዜው ይቆይ እንጂ ሃቁ መውጣቱ አይቀርም ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነ አብርሃ በላይ ፣ ከነ ስዬ አብርሃ ፣ ከነ ገብሩ አስራት መልስ ይጠብቃል። መልሱ ግን እንደ ከአሁን ቀደሞቹ የለበጣ ሳይሆን እውነተኝነትን ያቀፈ ሊሆን ይገባዋል። በዙ ገጽ ያለው ጽሁፍ በመጻፍ የምናውቀውን እንደገና ከሚነግሩን የማናውቀውንና የሚጠቅመንን ቢገልጹልን ትግሉን አንድ ምዕራፍ ወደ ፊት እንደ ማስኬድ ይቆጠራል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ
በልጅግ አሊ